02.5/755

03 ሰኔ 2008

ለ፡ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ለ፡ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ለ፡ የስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ለ፡ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ለ፡ የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ለ፡ የምግብ መጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

ለ፡ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት

ለ፡ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ኤጀንሲ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>*መመሪያ ስለመላክ ይመለከታል ፤*</u>

ሰኔ 2 ቀን 2008 ዓ/ም የፀደቀውን የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ “ሀ” የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ከዚህ ሸኝ ደብዳቤ ጋር በማያያዝ መላካችንን እናስታውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ተካልኝ ከድር መሐመድ
ህግ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

<u>እንዲያውቁት፣</u>

- ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለክቡር ሚኒስቴር ዴኤታዎች

<u>ግልባጭ፣</u>

- ለሁሉም ዳይሬክቶሬት
  <u>ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u>

# የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ ''ሀ''

# የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሠጣጥ

# መመሪያ ቁጥር 526/2013

ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

ሰኔ 2008ዓ/ም

# የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሠጣጥ መመሪያ ቁጥር 526/2013

መንግሥት፤ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ለሀገሪቱ ልማት የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማጎልበት ለዘርፉ የተለያዩ የማበረታቻና የታሪፍ ከለላ መስጠት አስፈላጊነቱ ስላመነበት፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተሳታፊ የሆኑ ወይም የሚሆኑ ድርጅቶች የታሪፍ ከለላ የሚያገኙበትን አግባብ በተመለከተ የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 45/2008 ያወጣ በመሆኑ፣

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን የመምራት ሕጋዊ ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑ፣

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፤የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 45/2008 አንቀጽ 8/ሰ/ መሠረት ተጠቃሚ ለሚሆኑት አምራች ኢንዱስትሪዎች የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሠጣጥ መመሪያ እንዲያወጣና ተግባራዊ እንዲያደረግ በሰጠው ውክልና መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ‹‹ በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት አሠጣጥ መመሪያ ቁጥር 526/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፣

2. " ኮሚቴ" ማለት ከሚኒስቴሩና ከተጠሪ ተቋማት የተውጣጡ አባላትን የያዘ የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" ተጠቃሚ ለመሆን የቀረቡ ጥያቄዎችን በመመርመር የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስትሩ ለማቅረብ በሚኒስቴሩ ሥር የተቋቋመ አካል ነው፣

3. " ተጠሪ ተቋማት" ማለት ተጠሪነታቸው ለሚኒስቴሩ የሆኑ ኢንስቲትዮዎች፣ ኤጀንሲዎች እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ናቸው፣

4. " የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል" ማለት በሚኒስቴሩ መሥሪየ ቤት ስር የተቋቋመ የሴክቶሪያል ግንኙነትና ማበረታቻ ዳይሬክቶሬት ነው፣

5. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 45/2008 አንቀጽ 3 መሠረትለሌሎች ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" ተጠቃሚነት የምሥክር ወረቀት በማግኘት ከውጭ የሚገቡ ግብዓቶችን ከቀረጥ ነጻ ወይም በዝቅተኛ ታሪፍ በማስገባት በሚያመርቱ አምራች ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት

# ኮሚቴ ስለማዋቀር፣ የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት እና የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

## 4. የኮሚቴው አወቃቀር

ሀ) ኮሚቴው ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሰብሳቢ እና ከተጠሪ ተቋማት በተውጣጡ አባላት ይዋቀራል፣

ለ) የኮሚቴው ሰብሳቢና አባላት በሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሆኖ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚሰየም አንድ ሰብሳቢ፣ ከየተጠሪ ተቋማቱ የሚሰየሙ አንድ - አንድ አባላት እና የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሴክቶራል ግንኙነትና ማበረታቻ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የኮሚቴው አባልና ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 5. የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" ተጠቃሚነት ሊበረታቱ የሚገባቸውን የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፎችና መስኮችን በጥናት ይለያል፣

ለ) የሚሰጡ የታሪፍ ከለላዎች በሀገር ውስጥ ያሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች ምርታማነት ላይ ወይም በአቅርቦትና ዋጋ አንጻር በኅብረተሰቡ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የማያስከትሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

ሐ) ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ወይም አግባብነት ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ወይም ማኅበራት ለሚቀርቡ የታሪፍ ከለላ ጥያቄዎች ወይም በራሱ አነሳሽነት ሊሰጡ ስለሚገቡ የታሪፍ ከለላዎችን በጥናት ይለያል፣

መ) የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" የታሪፍ አመዳደብ፣ ምጣኔ(rate) እና አጠቃቀም ላይ በተግባር የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመመርመር በሥራ ላይ ያሉ ሕግጋትና አሠራሮች እንዲሻሻሉ የውሳኔ ሐሳብ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣

ሠ) አገር ውስጥ በተፈላጊው ጥራትና መጠን ሊመረቱ የሚችሉ ምርቶችን በማጥናት በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ወደ አንደኛ መደብ ታሪፍ ከፍ ለማድረግ ለአገር ውስጥ ግብዓት ከለላ የሚሰጥበትን በጥናት ላይ የተመሠረተ የውሳኔ ሐሳብ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣

ረ) የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 45/2008 እና በዚህ መመሪያ መሠረት ተግባራዊ የሚሆነው የታሪፍ ከለላ በሥራ ላይ በቆየበት ጊዜ ከለላውን ተጠቃሚ የሆኑ የአምራች የኢንዱስትሪዎች ምርት ከውጭ ከሚገቡ ምርቶች ጋር ለመወዳደር የገነቡት አቅምና ዝግጅት በቂ መሆኑን በጥናት በማረጋገጥ ከለላው እንዲነሳ የውሳኔ ሐሳብ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣

ሰ) በአንደኛ መደብ የጉምሩክ ቀረጥ ላይ የሚያጋጥሙ የታሪፍ አመዳደብ ምጣኔ ችግሮችን በመመርመር አመዳደቡ እንዲስተካከል የውሳኔ ሐሳብ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣

ሸ) ኮሚቴው የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" ለገቡ ነባር ምርቶች ለመጠቀም ጥያቄያቸው ተቀባይነት ያገኙትን ድርጅቶችን አጣርቶ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች ሴርተፊኬት እንዲሰጣቸው ለምስክር ሰጪው አካል ያስተላልፋል፣

ቀ) ሰብሳቢው የኮሚቴው አባላት የተስማሙበትን የውሳኔ ሐሳብ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣

በ) በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" ሳልገቡ ምርቶችና ግብዓቶች የቀረበውን የውሳኔ ሐሳብ በሚኒስትሩ ተቀባይነት ካገኘ ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስትር ለውሳኔ ያስተላልፋል፡፡

## 6. የኮሚቴው የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

ሀ) ለሚኒስቴሩ የቀረበው የታሪፍ ከለላ ጥያቄ ሙሉ መረጃ ተሟልቶና በሚመለከተው ተጠሪ ተቋም የታሪፍ ከለላ ያስፈለገበት ወይም ሊነሳ የሚገባበት ምክንያት ተገልፆ በተጠሪ ተቋም የበላይ ኃላፊዎች በተፈረመ ደብዳቤ ተደግፎ ሲቀርብ የኮሚቴው ፀሐፊ የውይይት መነሻ ሐሳብ አዘጋጅቶ በ3 ቀን ውስጥ ተዘጋጅተውበት እንዲመጡ ለኮሚቴው አባላት ያስተላልፋል፣

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ መሠረት ፀሐፊው ያቀረበውን የመነሻ ሐሳብ ላይ የኮሚቴ ሰብሳቢው አባላትን ለስብሰባ በመጥራት ውይይት እንዲደረግ እና የውሳኔ ሐሳብ እንዲቀርብ ያደርጋል፣

ሐ) ስብሰባው የሚካሄደው ጥያቄ ያቀረበውን ድርጅት ጉዳይ አጣርቶ ጉዳዩን ለኮሚቴው ያቀረበው ተጠሪ ተቋም ተወካይ ሲገኝ እና ከአጠቃላይ ከኮሚቴው አባላት 2/3ኛው ሲገኙ ብቻ ነው፣

መ) ኮሚቴው ስብሰባ የሚያካሄድበትን የጊዜ ሰሌዳ ይወስናል፣

ሠ/ የውሳኔ ሐሳቦች ለሚኒስትሩ የሚቀርቡት በኮሚቴው ሰብሳቢና አባላት 75 በመቶ እና ከዚያ በላይ ሲደገፍይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የአምራች ድርጅቶች ጥያቄ አቀራረብ ፣ የተጠሪ ተቋማት እና የምሥክር ወረቀት ሰጪው አካል ተግባርና ኃላፊነት

## 7. የተጠሪ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) በየንዑስ ሴክተሩ ሊሟሉ የሚገባቸውን ዝቅተኛ የተጨማሪ እሴት ምጣኔዎች አጥንቶ ማቅረብና አስፈላጊ ሲሆን ክለሳ ለማድረግ የማሻሻያ ሐሳብ ለኮሚቴው ያቀርባል፣

ለ) አምራች ድርጅቶች የሚያቀርቡትን የተጠቃሚነት ጥያቄ ከዚህ መመሪያ እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 45/2008 አባሪ በሆኑት ቅጾች መሠረት አሟልተው ሲያቀርቡ በመመርመር ተቀባይነት ያገኙትን በመለየት ከተሟላ የጥናት ሰነድ ጋር ለኮሚቴው ያቀርባል፣

ተጠሪ ተቋማቱ ይህን ሲፈጽሙ የሚከተሉት ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል ፤

1. ግብዓቱ ላይ የተጣለው የታሪፍ ምጣኔ(rate)ና በመጨረሻ ምርቱ ላይ የተጣለው የታሪፍ ምጣኔ ልዩነት፣
2. አዲስ የከለላ ጥያቄዎች ከሆኑ ግብዓቶቹ ቀድሞ በሁለተኛ መደብ ያልተካተቱ መሆናቸውን፣
3. የቀረበው የታሪፍ ከለላ ጥያቄ ቀደም ሲል ከሁለተኛ ታሪፍ ምድብ ወጥቶ ወደ አንደኛ ታሪፍ ምድብ ያልተመለሰ መሆኑን ያረጋግጣል፣
4. ጥያቄ አቅራቢው ድርጅት የጠየቀውን ግብአት ተጠቅም የሚያመርተው ምርት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የመተካት እና የውጭ ምንዛሪን የማዳን ጠቀሜታ፣
5. የመንግስት የኢንዱስትሪ ልማት ትኩረት አቅጣጫ ጋር መጣጣሙን፣
6. ጥያቄ አቅራቢው ድርጅት የጠየቀውን ግብአት ተጠቅም በሚያመርተው ምርትላይ አገሪቷ ያላት የአዋጭነት ደረጃ ከፍተኛ መሆንና አለመሆን፣
7. የተጠየቀው ግብዓት ለኢንዱስትሪው መስክ አስፈላጊ መሆኑን፣
8. የከለላውን አስፈላጊነትና ሊሰጥ የሚገባውን የከለላ መጠን፡፡

ሐ) ለተጠሪ ተቋማቱ የሚቀርቡ የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ ‹‹ሀ›› ጥያቄዎች አገልግሎት የሚያገኙበትን ጊዜ በመወሰን በዜጎች ቻርተር በማካተት አገልግሎት ይሰጣል፣

መ) የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ ‹‹ሀ›› ላይ ያልተካተቱ ግብዓቶች በማጥናት እንዲካተቱ ለኮሚቴው ያቀርባል፣

ሠ) በአገር ውስጥ ግብዓት መመረት በመጀመሩ ወይም ትስስር መፍጠር የሚያስችል ሁኔታ በመፈጠሩ ከውጭ የሚገቡት ከጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ ‹‹ሀ›› ወጥተው በአንደኛ መደብ ታሪፍ ሊካተቱ በሚገባቸው ግብአቶችን ላይ ጥናት በማካሄድ የውሳኔ ሀሳብ ለኮሚቴው ያቀርባል፣

ረ) ኮሚቴው የባለሙያ ድጋፍ ሲፈልግ ባለሞያ በመመደብ ድጋፍ ያደርጋል፣

ሰ) የታሪፍ ከለላ የተሰጣቸው ኢንዱስትሪዎች ከውጭ የሚያስገቡት ግብዓት ለተፈለገው ዓላማ መዋሉን ያረጋግጣል፣ በየዓመቱ ያለውን ለውጥና መሻሻል ይከታተላል፣ የእነዚህን ውጤት ሪፖርት በየወቅቱ ለኮሚቴው ያቀርባል፣

ሸ) እያንዳንዱ ተጠሪ ተቋም እነዚህን ሥራዎች እየሰራ ለዋና ዳይሬክተሩ የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍል የተውጣጡ ባለሙያዎችን የያዘ የቴክኒክ ቡድን ያቋቁማል፣

ቀ) ከጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች ወደ አነስተኛና መካከለኛ ለተሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ ‹‹ሀ›› ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣

በ/ ከጨርቃ ጨርቅ እና ከቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩቶች ከ2005ዓ.ም ጀምሮ ዝርዝራቸው ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተላልፎ የሁለተኛ መደብ ‹‹ሀ›› ከለላ ተጠቃሚ ከሆኑት ውስጥ ከተቋቋሙ 3 ዓመት ያላለፋቸውና አነስተኛና መካከለኛ የሆኑት አገራዊ ኢንዱስትሪዎች ተለይተው እስካሁን ያለው አጠቃቀማቸው ተገምግሞ አጥጋቢ ከሆነ እንደሌሎቹ አስፈላጊውን አሟልተው ሲገኙ ያስተናገዳሉ፣

ተ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ " በ " በተጠቀሰው መሠረት 3 ዓመት ያለፋቸው እና የቀድሞው አምራች ድርጅት በሌላ ሰው ሥም የንግድ ፈቃድ አውጥቶ እንደገና በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ ‹‹ሀ›› ለመጠቀም የሚሞክሩትን ለመከላከል አስፈላጊውን የማጣራት ተግባራትን ያከናውናል።

## 8. የአምራች ድርጅቶች የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ ‹‹ሀ›› የተጠቃሚነት ጥያቄ ስለሚቀርብበት ሁኔታ

አምራች ድርጅቶች የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ ‹‹ሀ›› ተጠቃሚ ለመሆን ለተጠሪ ተቋማት ጥያቄ ሲያቀርቡ የሚከተሉትን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።

ሀ) ነባር የከለላ ተጠቃሚ ከሆኑ መቼ መጠቀም እንደጀመሩና ከለላው ያስገኘላቸውን ጠቀሜታ (ከምርት መጠን፣ ከገቢና ትርፋማነት፣ ከሰው ኃይል ቅጥር፣ ከእሴት ጭማሪ፣ ከፊትና የኋልዮሽ ትስስር፣ ወዘተ) አንጻር ዝርዝር መረጃ ማቅረብ፣

ለ) ከለላ የተጠየቀባቸው ምርቶችና የግብዓቶች የታሪፍ ቁጥሮች ማቅረብ፣

ሐ) ግብዓቱ ለሚያመርቱት ምርት አስፈላጊ መሆኑንና በአገር ውስጥ የሚመረት በጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ የሆነ ተመሳሳይ ግብዓት አለመኖሩ ማረጋገጥ፣

መ) የግብዓቶቹን መጠንና ስብጥር ማረጋገጥ፣

ሠ) ምርቱን ለማምረትየሚያስፈልግ አጠቃላይ ወጪና አንዱን ምርት ለማምረት የሚወጣው ወጪ ማቅረብ፣

ረ) ለአገር ውስጥ የሚያቀርበው ምርት ከውጪ የሚገባ ተመሳሳይ ምርትን ከመተካት አንጻር ያለበትን የተወዳዳሪነት ደረጃ እና የሽያጭ ዋጋ ማቅረብ፣

ሰ) ከለላ ከተሰጠ በኋላ ለኢንጂነሪንግ በ5ዓመታት፣ ለሌሎች ውስጥ በ3 ዓመታትበየዓመቱ በአገር ውስጥ የሚታከለው ተጨማሪ እሴት፣ የምርት ሂደቱ የሚያስገኘው የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የሚፈጠር የፊትና ኋልዮሽ ትስስር የሚያመለክት መረጃ ማቅረብ ናቸው።

## 9. የምሥክር ወረቀት ሰጪው አካል ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጠው የምስክር ወረቀት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ስር የተቋቋመው የሴክቶሪያል ግንኙነትና ማበረታቻ ዳይሬክቶሬት እንዲሰጥ ተወክሏል፣

ለ) ጥያቄ ለቀረበበት ምርት የሚያስፈልገው ግብዓት በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ “ሀ” ዝርዝር ውስጥ መኖሩን ያረጋግጣል፣

ሐ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ የታሪፍ አንቀጽ ለውጥ መኖሩን ያረጋግጣል፣ ለዚህም አስፈላጊ ሲሆን የባለሥልጣኑን የሙያ እገዛ ይጠይቃል፣

መ) ጥያቄ የቀረበባቸው ምርቶች በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ ‹‹ሀ›› መሠረት ተጠቃሚ ለመሆን የማያስችሉ ሥራዎች ውስጥ አለመሆናቸውን ያረጋግጣል፣

ሠ) የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ ‘’ሀ’’ አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 45/2008 አንቀጽ 8፣ 10 እና 11 የተዘረዘሩት መስፈርቶችና ቅድመ-ሁኔታዎች እንዲሁም ዝቅተኛው የተጨማሪ እሴት ምጣኔ መሟላታቸውን በማረጋገጥ የጉምሩክ ታሪፍ መደብ ተጠቃሚነት የምሥክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያሻሽላል ወይም ሳይሟሉ ሲቀሩ ወይም ከለላው ሲነሳ ይከለክላል፣ ይሰርዛል ወይም ያግዳል፣

ረ) የብሔራዊ የስታንዳርድ የግብዓት ምርት ጥመርታ ላልተዘጋጀላቸው ምርቶች በተጠሪ ተቋማት ተዘጋጅተው ወይም ተገምግመው የሚቀርቡትን የግብዓት-ምርት ጥመርታዎችን በማየት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

ሰ/ የምሥክር ወረቀት የተሰጣቸውን፣ ማሻሻያ የተደረገባቸው፣ የታደሰላቸው ወይም የተሠረዘባቸው አምራች ድርጅቶች ዝርዝር የተረጋገጠ የምሥክር ወረቀት ኮፒና ሌሎች አባሪ ሰነዶችን ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንና ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 10. ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት የአገልግሎት ዘመንና ክፍያ

ሀ/ የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ለማውጣት ብር 300 ለማሳደስ ወይም ለማሻሻል ብር 150 የአገልግሎት ክፍያ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መክፈል ይኖርበታል፣

ለ/ የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ "ሀ" ተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ወይም ከታደሰበት ጊዜ ጀምሮ ለአንድ ዓመት ብቻ ያገለግላል።

### 11. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ በሚኒስቴሩ ሊሻሻል ይችላል።

### 12. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ

አህመድ አብተው

ኢንዱስትሪ ሚኒስትር

1.<u>የጉምሩክ ታሪፍ ከለላ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ በሆኑ የሚሞላ</u>

ድርጅቱ ከለላውን መጠቀም የጀመረበት ጊዜ (ቀን፣ወር፣ዓ.ም)------------------------------
-

1.1 የተፈጠረ ትስስር፡-

1.2.1የፊትዮሽ (ማስፋፊያ ፕሮጀክት ፣ግብዓት አቅራቢዎች መቀበልና --------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------

1.2.2 የኃልዮሽ (ማስፋፊያ፣ ከግብዓት አቅራቢዎች መቀበልና ሌሎች)--------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------

1.2.3 የጎንዮሽ (ፓኬጂንግ እና ሌሎች)------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------

2. ከለላ ከተሰጠ በኃላ በቀጣይ 3 አመት (5 ዓመት ለኢንጅነሪንግ ኢንዱስትሪዎች) ፡-

2.1 የምርት ሂደት የሚያስገኘው የቴክኖሎጂ ሽግግር-----------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
---------------------------------------------------------

2.2 የሚፈጠሩ ትስስሮች-----------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------

2.3 የሚፈጠር የፊትና የኃልዮሽ ትስስር---------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------